የሰ/መ/ቁጥር 27783

ሐምሌ 05 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ አብዱራሂም አህመድ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ እናትነሽ ከተማ ጠበቃ አቶ መኮንን አምቦ ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- ወ/ሮ ፋንታዬ መሐመድ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማ/ብሔ/ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ ሥልጣኑ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የነገሩም መነሻ የአሁን መልስ ሰጭ ሚስትነታቸው እና የልጆች የአሁኑን አመልካችን ጨምሮ ሞግዚትነት ሥልጣን ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለወረዳው ናዒባ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ጉዳዩ ታይቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 09/94 ሐምሌ 09 ቀን 1994 ዓ.ም ማስረጃው ተሰጥቷቸዋል፡፡

ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች 1ኛ እኔ በሌለሁበት፣ በውጭ አገር የተሰጠ ማስረጃ በመሆኑ፣ ሁለተኛ ጉዳዩ በሀይማኖታዊ ፍ/ቤት ቀርቦ የታየ ሲሆን በማስረጃው ላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 700 መጠቀሱ አግባብነት የለውም በሚል ለቃዲ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርባለች፤ የቃዲው ፍ/ቤትም ለውሣኔው መሠረት የሆነው ህግ ከቅዱስ

ቁርዓን ውጭ የተጠቀሰ በመሆኑ የናዒባው ፍ/ቤት አስተካክሎ ይወስን ዘንድ መልሶታል፡፡

በዚሁ መሠረት የናዒባው ፍ/ቤት ጉዳዩን እያየው እያለ የአሁን መልስ ሰጭ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት ሊታይ ይገባዋል በሚል ሲከራከሩ፤ አመልካች በበኩሏ በሸሪዓ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 188/92 ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ይኸው ሃይማኖታዊው ፍ/ቤት ነው በማለት ተከራክራለች የናዒባው ፍ/ቤትም ይህንን የአመልካችን ክርክር ተቀበሎ አስቀድሞ በአሁን መልስ ሰጭ ጠያቂነት በናዒባው ፍ/ቤት የታየ ጉዳይ እስከሆነ ድረስ በተጀመረው በቅዱስ ቁርዓን ህግ መሠረት ሊታይ ይገባዋል እንጂ በመደበኛ ፍ/ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት በቅዱስ ቁርዓን ህግ መሠረት መልስ ሰጭ አንድ ስምንተኛ ንብረት ይወስዳሉ ሲል መጋቢት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ የአሁን መልስ ሰጪ ለቃዲው ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው የቃዲ ፍ/ቤት ጉዳዩን በሃይማኖታዊ ፍ/ቤት ለማየት የሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡ መልስ ሰጭ በዚሁ መሠረት ጉዳዩ በናዒባው ፍ/ቤት እንዲታይ ፈቃድ የላቸውም ስለሆነም ጉዳዩ ሊታይ የሚገባው በመደበኛው ፍ/ቤት ነው ሲል ዳኝነት ሰጥቷል፡፡

በዚሁ የቃዲ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት መልስ ሰጭ ሚስትነታቸው እና የልጆቻቸው ሞግዚትነት ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ለዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይኸው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ በሥ/ፋ/መ/ቁ. 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም የሚስትነትና የልጆች ወራሽነትን ማስረጃ ሰጥቷቸዋል፡፡

አመልካችም ከላይ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የቃዲው ፍ/ቤት ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንጂ በሸሪዓ ህግ መሠረት ሊዳኝ አይገባውም ሲል በሰጠው ውሣኔ የይግባኝ

አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ይኸው ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ በመ/ቁ. 02219 ሰኔ 16 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት የዳንግላ ወረዳ ናዒባ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

ከዚህም ሌላ የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት በሥ/ፋ/መ/ቁ. 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም የመልስ ሰጭን ሚስትነትና የልጆችን ወራሽነት በማረጋገጥ የሰጠው «ውሣኔ» ይሰረዝለት ዘንድ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሠረት አቤቱታ አቅርባለች፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም በዚሁ ነጥብ ላይ ካከራከረ በኋላ መልስ ሰጭ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ የናዒባ ፍ/ቤቱ ሐምሌ 09 ቀን 1994 ዓ.ም ሚስትነታቸውን አረጋግጦ ውሣኔ ከሰጣቸው በኋላ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ለሁለተኛ ጊዜ ለዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው በፍ/ት/መ/ቁ. 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም በዋለው ችሎት በድጋሚ የሚስትነት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ስለሆነም ይህ ለሁለተኛ ጊዜ በመደበኛው ፍ/ቤት የተሰጠው የሚስትነት ማስረጃ (ውሣኔ) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360(2) መሠረት ሊሰረዝ ይገባዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነውም ይኸው ውሣኔ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለአዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ቀደም ሲል በዳንግል ወረዳ ፍ/ቤት በሥ/ፋ/መ/ቁ. 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ መሰረዙ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን ከመረመረ በኋላ ቀደም ሲል የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሰጠው ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአሁን አመልካች ሐምሌ 09 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ

ገብቼ እንድከራከር ይፈቀድልኝ በማለት መጠየቁን ተረድተናል፡፡ እንዲሁም ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት በአስተዳደራዊ ሁኔታ አቤቱታ አቅርበው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አንድ ጉዳይ በሁለት የተለያዩ ፍ/ቤቶች ሊታይ አይገባውም ስለሆነም ክርክሩ ሊቆም ይገባዋል ሲል የፃፈ መሆኑንም ካቀረባቸው ማስረጃ ተረድተናል፡፡ ይህም ከሆነ የወረዳው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አመልካች በወረዳው ፍ/ቤት ጉዳዩ እንደነበረ ታውቃለች፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ክርክር መደረጉን ለማያውቅ ወገን እንጂ እንደ አመልካች አቤቱታ ያለውን ሊሸፍን አይችልም፡፡ አመልካች ያለአግባብ ጣልቃ ልትገቢ አይገባም ተብላ ከሆነ በየደረጃው በይግባኝ እንዲስተካከል ማድረግ ከምትችል በቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ ማቅረብ አትችልም፤

እንዲሁም የአሁን መልስ ሰጭ ያቀረበችው አቤቱታ የሚስትነት መብትን ለማረጋገጥ በመሆኑ ከጉዳዩ ይዘት አንፃር የክርክር ተካፋይ የግድ ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው ደግሞ የክርክር ተካፋይ መሆን እየቻለ ተካፋይ ሳይሆን ውሣኔ ተሰጥቶ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች የግድ የክርክር ተካፋይ ናት ማለት አይቻልም የሚሉትን ሁለት ምክንያቶች መሠረት አድርጐ የወረዳው ፍ/ቤት ቀደም ሲል የሰጠውን ውሣኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ለጠ/ፍ/ቤቱ ባቀረበችው የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ይኸው ፍ/ቤት ሁለቱንም ወገኖች አከራክሮ በተመሳሳይ ምክንያት የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይህ በከፍተኛው ፍ/ቤት እና በጠ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት ነው የሰበር አቤቱታ ያቀረበችው፡፡ የሰበር አቤቱታው ይዘት በሥር ፍ/ቤቶች ከቀረበው የተለየ አይደለም፡፡

በዚህም ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶች የተነሳውን ክርክር በየፊናቸው በማጠናከር የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር በአዲስ መልክ የተጠቀሰ ክርክር የለውም፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ የመዝገቡ ግልባጭ እንደሚያስረዳው መልስ ሰጭ የሟች ከተማ ኢብራሂም ሚስት ናት ወይስ አይደለችም? የሚለውን በሚመለከት በሁለት የተለያዩ ፍ/ቤቶች ታይቶ በተለያየ ጊዜ ሚስት መሆኗን የሚያረጋግጥ ውሣኔ /ማስረጃ ተሰጥቷል፡፡ ሁለት የተለያዩ ፍ/ቤቶች ሲባልም በግዛት ክልል ምክንያት የተለያዩ ሳይሆን የመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ፍ/ቤት ሲሆን ሌላው መደበኛው ፍ/ቤት መሆኑ ጭምር ነው፡፡ ሁለቱም ፍ/ቤቶች የሰጡት የሚስትነት ማረጋገጫ የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤት የተለያዩ መሆኑም ለዚህ ክርክር ምክንያት ሆኗል፡፡ ይኸውም በናዒባው ፍ/ቤት የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ከሟች ሀብት የሚስት ድርሻ 1/8ኛ መሆኑን የሚጠቅስ ሲሆን የመደበኛው ፍ/ቤት ማስረጃ ደግሞ ግማሽ የሀብት ድርሻ የሚያስጠብቅ ነው፡፡ ሚስትነትን የሚያረጋግጠውን ማስረጃ በሚመለከት በሁለቱም ዓይነት ፍ/ቤቶች በእየርከኑ በተቀመጡት ደረጃ በደረጃ ታይቶ በስተመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው፡፡ ይኸውም የክልሉ ጠ/ሸሪዓ ፍ/ቤት የናዒባ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽደቅ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ደግሞ የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት በሥ/ፋ/መ/ቁ 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶ ወስኗል፡፡ በሁለቱም ዓይነት ፍ/ቤቶች በተለያዩ አኳኋን የተሰጠውን ውሣኔ በአንድ ጊዜ ማስፈፀም ወይም ህጋዊ ውጤት እንዲኖረው ማድረግ የሚቻል አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 8 መሠረት የሚቀርበው የመቃወሚያ ክርክርም አስፈላጊነት በመጨረሻ ለማስፈፀም የሚያስቸግር ውሣኔ በተለያዩ ፍ/ቤት እንዳይሰጥ ለማድረግ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(2)(ሐ) መሠረት መቃወሚያ ሊቀርብ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ

አንድ ጉዳይ በተለያዩ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባውም የሚለው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በዚሁ ሕግ ቁጥር 244 መሠረት መቅረብ የሚገባው ቢሆንም በዚሁ መቅረብ በሚገባው ጊዜ ሳይቀርብ የቀረው የመቃወሚያ ክርክር ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክል ሆኖ ከተገኘ ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊነሳ እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(3) ተደንግጓል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 8 መሠረት በማድረግ የሚቀርበው የመቃወሚያ ዓይነት ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክል በመሆኑ በፍ/ቤቱ በሌላው ወገን ጠያቂነትም ሆነ በእራሱ አነሳሺነት እንደተረዳው ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊቀበለው ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት የአሁን አመልካች ይህንኑ መሠረት በማድረግ የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ሐምሌ 09 ቀን 1995 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በጉዳዩ ላይ ጣልቃ ልገባ ይገባል በማለት የጠየቀች ለመሆኑ ከውሣኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡

የወረዳው ፍ/ቤት ይህንኑ እንደተረዳ በእርግጥም አንድ ጉዳይ በተለያየ ፍ/ቤት የቀረበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፍርድ በፊት አጣርቶ ሊወስን ይገባው ነበር ይህንን አለማድረጉ በክርክር አመራር ረገድ ሥነ-ሥርዓታዊ ግድፈት ፈጽሟል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበላቸውን ጉዳይ ከዚህ አንፃር መመልከት ሲገባቸው ከውሣኔ በፊት ስለ ክርክሩ ያወቀ ወገን በመጨረሻ ውሣኔው ላይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 ን መሠረት በማድረግ መቃወሚያ ማቅረብ አይችልም በሚለው ምክንያት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የህግ ምክንያት ጉዳዩ በሌላ ፍ/ቤት ቀርቦ እየታየ የሚለውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን በዚህ

ጉዳይ ይህ ሌላ የተባለው ፍ/ቤት መልስ ሰጪ በመጀመሪያ አቤቱታ ያቀረበበት ፍ/ቤት በሃይማኖታዊ ህግ መሠረት የሚዳኝ የሸሪዓ ፍ/ቤት በመሆኑም ጭምር ሌላ የህግ ክርክር የሚያስነሳ ነው፡፡

ጉዳዩ ለመደበኛው የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት ከመቅረቡ በፊት በአሁን መልስ ሰጪ አቤቱታ አቅራቢነት በናዒባ ፍ/ቤት ታይቶ የመልስ ሰጭ ሚስትነት በማስረጃ ተረጋግጦ በዚሁ ፍ/ቤት የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አግኝታለች፡፡ አከራካሪ የሆነውም ጉዳይ የሚስትነት ማስረጃን የሚመለከት ነው መልስ ሰጭም በመጀመሪያ በእራሷ አነሳሺነት ይህ አከራካሪ የሆነውን ጉዳይ በተመለከተ አቤቱታው ታይቶ የሚስትነት ማስረጃ እንዲሰጣት በናዒባ ፍ/ቤት የማቅረቧ ተግባር በእራሱ ስለጉዳዩ በሸሪዓ ህግ መሠረት በየደረጃው ባሉት የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት የፈቀደች ለመሆኑ አረጋጋጭ ነው፡፡ ፈቃድ ክስ በማቅረብ ተግባር የሚገለጥ ነው፣ ከሳሽን በሚመለከት አንድ ጊዜ በሸሪዓ ህግ መሠረት ለመዳኘት ፈቅዳ ክስ አቅርባ ውሣኔ ባገኘችበት ጉዳይ እንደገና ለመደበኛው ፍ/ቤት ተመሳሳይ ዳኝነት መጠየቋ ሲታወቅ መደበኛው ፍ/ቤት በሌላ በህግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ እየታየን ያለ ጉዳይ በድጋሚ ለመመልከት የሚያስችል ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበት ይገባው ነበረ፡፡

የግል እና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖት ህጐች መሠረት መዳኘትን አይከለክልም በማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግሥት በአንቀጽ 34/5/ ተደንግጓል፡፡ በሃይማኖታዊ ህግ በሸሪዓ ፍ/ቤት ለመዳኘት ፈቃድ ሰጥቶ ዳኝነት የጠየቀ ወገን መሆኑ ከታወቀ ይህንኑ ውሣኔ ያገኘበትን ጉዳይ በሚመለከት በመደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ እንዲታይ ማድረግ የሚቻል ስላለመሆኑም በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ 4 ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 በተመለከተው ፍትህ የማግኘት መብት በሚለው ሥር « ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ

በህግ የደኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው የሚደነግግ እንጂ በህግ የመዳኘት ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል አቅርቦ ዳኝነት ካገኘ በኋላ እንደገና ተመልሶ በዚያው ጉዳይ በፍርድ ቤት ጉዳዩን አቅርቦ ማስወሰን እንዲቻ ድርብና አስፈላጊ መብት የሚሰጥ ድንጋጌ አይደለም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት የአሁን መልስ ሰጭ በሃይማኖታዊው ህግ መሠረት በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ለመዳኘት ፈቃድ ሰጥታ ውሳኔ ካገኘች በኋላ እንደገና ሐሳቤን ቀይሬያለሁ፣ በመደበኛ ፍ/ቤት ልዳኝ ይገባል በማለት በመደበኛው ፍ/ቤት ክስ ማቅረቧ ሲረጋገጥ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ክሱን ውድቅ ማድረግ ሲገባው ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፋ.ቁ. 04278 ታህሳስ 04 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07903 ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡
2. የዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 00559/96 መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት መልስ ሰጭ በናዒባ ፍ/ቤት የሚስትነት ማረጋገጫ ውሣኔ ማግኘቷ ሳይታወቅ በዳንግላ ወረዳ ፍ/ቤት በድጋሚ በሥ/ፋ/ት/መ/ቁ 361/95 ሐምሌ 11 ቀን 1995 ዓ.ም ታይቶ የተሰጠው የሚስትነት ማረጋገጫ ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት ተሰርዟል ሲል የሰጠው ብይን ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ